# የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያ

**የአዲስ አመት ዋዜማ**

የአዲስ አመት ዋዜማን December 31 ከ 5 p.m. ጀምሮ እናከብራለን። ምግብ ይኖረናል፣ የጸሎትና የአምልኮ ጊዜ ይኖረናል፤ ቲሸርት ይዘጋጃል፤ የስነ-ጽሐፍ ጊዜ ይኖረናል። ስነ-ጽሑፍ ለማቅረብ የምትፈልጉ ለረድኤቱ አስታውቁ። ስዎችን ጋብዙ። ጌታ ይባርካችሁ።

**የአገልግሎት ጥሪ**

በተለያየ መስክ ለማገልግለ የምትፈልጉ ሽማግሌዎችን አነጋግሩ።

**የአርብ ፕሮግራም**

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ።

**እርስ በርስ እንተያይ**

የጀምርነውን ለሌሎች ወገኖቻችን የመደወል እና እርስ-በእርስ የመጠያየቁን ነገር አጥብቀን እንድቀጥል ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። በዚህ አገልግሎት እየተጋችሁ ያላችሁ ወገኖች እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
**773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)**
**773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)**
**630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)**
**773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)**
**773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)**

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10

# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!




"የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ..."
(ቆላ. 3:16)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**November 17, 2019** | **ሕዳር 7፣ 2012 ዓ.ም.**

# የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

**ጸሎት** ............................ ወንድም ሲሳይ መሸሻ

**አምልኮ**.......................... የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

**ፕሮግራም መሪ** ............. ወንድም ረድኤቱ ካሳ

**ቃል** ............................. ወንድም ፍቅሩ ካዩ

**ማጠቃለያ** ...................... ወንድም ረድኤቱ ካሳ

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

“የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም።”
(ኢያሱ 1:8)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ሲሳይ መሸሻ | | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ኮከቤ አስረስ | | |
| ወ/ም ዘሪሁን/ዮሐንስ | | |
| ወ/ም አያሌው/ጸደቀ | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

## መንፈስ ቅዱስ አሳሳቢ (አስታዋሽ) መንፈስ

*“አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ... እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል” (ዮሐ. 14፡26)።*

መንፈስ ቅዱስ ግሩም አስተማሪ ነው። መንፈስ ቅዱስ በአብ ውስጥ ያለውን ስለሚያውቅ የጠለቀውን የቃሉን ፍቺ ያበራልናል። እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ቅዱስ የቃሉ ደራሲ ስለሆነ በቃሉ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ኃሳብ ለቅዱሳን ያሳውቃል። ስለዚህም ወደ መንፈስ ቅዱስ የበለጠ ስንቀርብ እግዚአብሔርን የበለጠ እያወቅን እንሄዳለን። መንፈስ ቅዱስ የቃሉ አስተማሪ ብቻ ሳይሆን ቃሉንም የሚያሳስብ መንፈስ ነው።

መንፈስ ቅዱስ አሳሳቢ (አስታዋሽ) መንፈስ ነው። በውስጣችን ያለውን ቃል በሚያስፈልገን ጊዜ ወደ ልባችን የሚያመጣው መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህም ቃሉ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ ያስተማረንን ሁሉ “ያሳስባችኋል” (የሐ. 14:26) ይለናል። በዚህ ቃል ዋስትና ወንጌላዊያኑ ኢየሱስ ያስተማረውን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አስታውሰው ጻፉልን። እንዲሁም በአገልግሎታቸው ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የጌታን ቃል ያስታውሳቸው ነበር። ለምሳሌ ሐዋሪያው ጴጥሮስ በመቶ አለቃ ቆርኖሊዮስ ቤት ወንጌልን ከሰበከ በኋላ በአሕዛብ ላይ መንፈስ ቅዱስ መውረዱን መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ወደ ልቡ በማምጣት አረጋገጠለት። ሐዋሪያው ስለዚህ ሁኔታ “ዮሐንስ በውኃ አጠመቀ እናንተ ግን በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ያለውም የጌታ ቃል ትዝ አለኝ” በማለት እንዴት መንፈስ ቅዱስ ለነበረበት ሁኔታ ቃሉን እንዳስታወሰው ጽፏል (ሐዋ. 11:16)። እንዲሁም ጌታ ስለሞቱና ስለ ትንሳኤው የተናገረውን እንዲሁም በትንቢት ስለ እርሱ የተጻፈውን ለሐዋሪያቱ ያሳታወሳቸውና ያበራላቸው መንፈስ ቅዱስ ነው (ዮሐ. 2:22፤ 12:16)።

ዛሬም ከቃሉ የተማርነውን እውነት የሚያስታውሰን መንፈስ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል በሙላት እንዲኖርብን ያዘናል (ቆላ. 3:16)። የእግዚአብሔር ቃል በሙላት በውስጣችን ካለ በሚያስፈልገን ግዜ መንፈስ ቅዱስ ለጊዜው የሚሆነውን ቃል ያሳስበናል (ያስታውሰናል)። በቃሉ የተሞላን ሰው መንፈስ ቅዱስ በማንኛው ሁኔታ የሚያስላስለውን ቃል ያሳስበዋል። ቃሉን በቀንና በሌሊት የሚያስብ ሰው “በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች፥ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል፤ የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል” (መዝ. 1:3)። እንዲህ አይነቱ ሰው በማንኛው ሁኔታ ውስጥ አይሰጋም፤ ደስታው ሙሉ ነው፤ ሁልጊዜም ፍሪያማ ነው። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ እንዲህ ያለው ሰው በቃሉ ውስጥ ስለሚኖር ነው። ለለዚህ እግዚአብሔር ለኢያሱ የሰጠው ዋና ምክር “የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም” (ኢያ. 1:8) የሚል ነው።

ወገኖቼ፡- በእግዚአብሔር ቃል ውስጣችን ከተሞላ መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ያስተውሰናል። ቃሉ በሙላት ከሌለበን ግን መንፈስ ቅድስ የሚያስታውሰን ነገር አይኖረውም። ምክንያያቱም ለማስታወስ የሚንችለው በውስጣችን ያለውን ነው። ቅዱሳን ቃሉ በሙላት ይኑርብን። በቃሉ እንጽናናለን፣ ጠላቶቻችንን ድል እንነሳለን፣ ጸንተን እንቆማለን። አሜን!